ፍትህን ፍለጋ!

# ፍትህን ፍለጋ!



(ለአበራ የማነአብ)

ርግብ ሆነህ በረህ...፣
አድማስን አቋርጠህ፣
ለሰላም፣ ለፍትህ፣ ለሕዝብ ክብር ስትል፣
በዘምባባ ቀንበጥ ጠመንጃን ልታስጥል፣
ቆርጠህ መምጣትህን በገቢር ሲረዱ፣
ጠመንጃ አምላኪዎች በፍርሃት ሲርዱ፣
ያገዱህ መስሏቸው ከቆራጥ ትግልህ መስክ፣
በፈሪ ልባቸው ተናንቋቸው እልክ፣
አወረዱህ አሉ? ከርቸሌ ወህኒ ቤት፣
የነርሱ መኖሪያ መሆን ወዳለበት!

አልተረዱም እንጅ፣
ግብርህ እንደ ስምህ ደምቆ እንደአበራ።
አላወቁም እንጅ፣
ትግልህ ለብዙኃን መንገድ እንደመራ።
አልገባቸውም እንጅ፣
የዓላማህ ጽናት ጀግና እንደሚያፈራ።

ቢረዱማ ኖሮ ልብ ቢኖራቸው፣
ህሊና ቢገዙ ሃቁማ ቢያንቃቸው፣
በሕዝብ ተተፍተው እርቃናቸውን ቀርተው፣
መች ይኖሩ ነበር በቁማቸው ሞተው!

ህሊናቸውን ሸጠው፣ ሥጋቸውን ሸጠው..፣
                    ነፍሳቸውን ሸጠው...
ህይወት-አልባ አካል ሬሳ ታቅፈው፣
አማላጅ በሆኑ ከርሳሞች... ተገዝተው፣
በሆድ ሊደልሉህ ያገር ሃቅን ክደው።

«እምቢኝ አሻፈረኝ... ከርቸሌ ይሁን ቤቴ፣
ያሜሪካ ኑሩ... ምኞት ነው ጠላቴ...፣»
ብለህ መለስካቸው? ሃፍረት አሸክመህ?!
ለሕዝብ ልዕልና ለፍትህ ወግነህ!!

እንሱ «እንደኖሩት» መኖር እንዳትሻ
ቆርጠህ ስትነግራቸው፣
ከፊትህ የቆመው በድን አካላቸው፣...
ምናለ ሬሳቸው?!

ትቢት፣ መሃይምነት፣ ጨለማ ጠመንጃ...
ለተጋረጣቸው፣
ክፋት፣ ምቀኝነት፣ በቀል፣ ዘረኝነት...
ለሰረጸባቸው፣
መልካም ትምህርት ልትሰጥ...፣
ቁምነገር ልትሰራ፣
የሻማ ብርሃን ፀዳል ልታበራ፣
ርግብ ሆነህ በረህ፣ አድማስን አቋርጠህ፣
ወይራ ዝንጣፊ፣ ዘምባባ ታቅፈህ፣
ለነጻነት ክብር ልትከፍል ዋጋ፣
ወህኒ ቤት ሳለኸው ፍትህን ፍለጋ::

ጌታቸው አበራ
1989? ዓ.ም.
(አምስተርዳም - ሆላንድ)

---

ይህቺ ግጥም የተጫረችው ከዛሬ አሥር ዓመታት በፊት ነው:: በቅርቡ ገጣሚው ባሳተመው *«ሕዝባዊ ማዕበል..»* በተሰኘው የግጥም መድበል *ሁለተኛው ዕትም* ላይ ወጥታለች:: አቶ አበራ የማነአብ እና ከእርሳቸው በፊትም ሆነ በኋላ የታሰሩ አያሌ የፖለቲካ እስረኞች ከ«ባዶ ስድስት» የስውር እስር ቤት . . . እስከ ክርቸሌ ድረስ አሁንም ድረስ በግፍ ታጉረው በመሰቃየት ላይ ይገኛሉ:: ትግላችን እስከወዲያኛው ቀጥሎ፣ በአዲሱ ዘመን የኢትዮጵያ እስር ቤቶች በሙሉ፣ ወደ ትምህርት ቤትነት እንዲቀየሩ መጣር ይኖርብናል::

G_ABERA@HOTMAIL.COM